# ድመት መንኩሳ  አመልዋ አትረሳ

## ይድረስ ለካሃዲዎቹ ይሁዳዎች

ኢትዮጵያ  ኣገራችን  በዓለም ታሪክ  ውስጥ ከፍተኛ  ስልጠኔ  ከነበራቸው ታላላቅ መንግስታት ውስጥ ኣንዳዋ ነበረች፡፡  ከዓመተ ዓለም ጀምሮ እስከ  ስድስተኛ ክፍለ ዘመን ገናና ከነበሩት መንግስታት ከነ ባዛንታይን፣፡ ፔርሺያ፣ ሮም ቻይና፣ እኩል ተሰልፋ   በሃያልነትዋ  ትታወቅ   እንደነበረች የታሪክ   ድርሳናት  አበክረው ይናገራሉ፡፡

ሆኖም ስልጣኔዋና ዕድገትዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ መጥቶ የዓለም መዛበቻ ሆነች፡፡ በድርቅ በጦርነት መታወቅ ልማድ ሆነ፡፡ በስልጣን የነበሩ ገዢዎች ደግሞ ከህዝብና  አገር  ጥቅም   ይልቅ  የግል  ጥቅማቸው  በማስቀደም  የግል  ዝናቸውን አጉልተው ለማሳየት ጥረት  ከማድረግ ውጭ የህዝቦች  ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተረግጠው ዜጎች  እንደ ዜጋ የማይቆጠሩበት የጥቂት አምባገነኖች የአንድ በሂር ህዝብ የበላይነት የተረጋገጠበት አገር አድርጓት ነበር፡፡

ይሁን እንጂ በህዝቦች የተቀናጀ  ትግል  ዘውዳዊ ስርዓት ከተገረሰሰ በኋላ ጠንካራ የፖለቲካ ፖርቲ ባለመኖሩ ተደራጅቶ የነበረው ወታደራዊ ሃይል ስልጣን ያዘ፡፡ በመሰረቱ  ዴሞክራሲያዊ  መንግስት  ያልነበረን  ወታደራዊ  መንግስት  በወቅቱ ተፈጥረው   የነበሩት   የፖለቲካ   ፓርቲዎች   በዓይነ   ቁራኛ   በመመልከት ጨፈጨፋቸው፡፡  የፖለቲካ  ፓርቲዎችም  የእርሰ  በርስ  ሽኩቻ  ዕድሜያቸውን አስጠሩት፡፡ ሁለቱም ተዳምረው ዕድሜ ፆታ፣ ትምህርቲ ሳይለይ ፋሽሽት ወታደራዊ መንግስት ዜጐች ወጥተው ሳይመለሱ አስቀራቸው፡፡ ወላጅ ያለ ልጅ ሽማግሌ ያለ ጧሪ መና አስቀራቸው ከአንድ ቤተሰብ 4  ሰዎች  በአንድ ጨረቃ  ርህራሄ በሌላው አረሜናዊ  ሰይፍ ገደላቸው፡፡  ቤተሰብ  እንደ ቤተሰብ ኣጠፋ፡፡  የዘር ማጥፋት ሂደት  አይደለም ይባል የሆን? እንጃ!

ይህም ፋሽሽታዊ ስርዓት በሰፊው የህዝብ ትግል ከተወገደ  በኋላ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ለአንድነታቸው ያደረጉትን ትግል ሰምሮ ዋስትና ቃል ኪዳን የሚሆናቸው በመፈቃቀድ በመከባበር በመቻቻል ህገ መንግስት አፀደቁ፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና  ህዝቦች  ህገ መንግስት  የአገሪቱ የበላይ ህግ ሆኖ ተቀረፀ፡፡ የህግ የበላይነት ተረጋገጠ፡፡ በእኩልነት በመፈቃቀድ በመከባበር በመቻቻል አንድነትዋ የጠነከረ ፌደራላዊት ዴሞክራሲያዊት ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ ተመሰረተች፡፡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሕገ መንግስቱና የህግ የበላይነት ለሚያከብሩና  ለሚያስከብሩ ዜጎች ያለ ገደብ ተሰጠ፡፡

እያንዳንዱ ብሄርና ብሄረሰብ የራሱን ዕድለ በራሱ የመወሰን መብት ተሰጠው፡፡ ቋንቋው ባህሉ ማሳደግ፣ በቋንቋው የመፃፍ የመዳኘት የመማር የስራ ቋንቋ የማድረግ ያልተገደበ መብት ተሰጠው፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 39 ሰፈረ፡፡ ህብረ ቀለማችን ውበታችንና የአንድነታችን መግለጫ ሆነ፡፡

እያንዳንዱ ቀበሌ የልማት የትምህርት፣ የጤና፣ የመብራት ስልክ  የመንገድ የንፁህ ውሃ  ተጠቃሚ  የሚያደርግ  ፖሊስ ተነድፎ  በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ህዝቦቻችን  በትግላቸው ያገኙት እሴትና የመንግስት ዴሞክራሲያዊ አመራርና ቁርጠኝነት  ያስመሰከረ ነው፡፡

የአገራችን በጎ ገፅታ ለዓለም ህዝብ ለማስተዋወቅ መንግስት ፣ ህዝብና የኢትዮጵያ ወዳጆች ያደረጉትን ያላሰለሰ ጥረት ሰምሮ በዓለም ላይ ደምቆና አሸብርቆ ታየ፡፡ የኢትዮጵያ ህዳሴ ተባለ፡፡ ኢትዮጵያዊያን  ደግም  በዓለም ላይ ማንነታችን ማረጋገጥ  ቻልን፡፡ በኣዲሱ ሚሌኒየም ፡፡

ብዙ ህብረ ቀለም፣ ብዙ ህዝብ አንድ አገራዊ ራእይ ተረጋገጠ፡፡ ተስፋ ሰጪ ሁለገብ ኤኮኖሚያዊ ዕድገት፣ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ጐራ ሊያሰልፉ የሚችል እሞቦቆቁላ የሚስጐመጅ ዕድገትና ራእይ በ 16 ዓመት ተፈጠረ፡፡ ብዙና ከንቱ

ትንቢያና የተቀናጀ  የከሃዲዎች ሴራ የከሸፈበት የአገራችን አንድነት የተረጋገጠበት ምዕራፍ ሆነ፡፡

ይህ ከብዙ በጥቂቱ ቀረበ እንጂ በአገራችን ያለው ለውጥ ባለፉት 100 ዓመታት ተሰርቶ፣ ተሰምቶ ታይቶ የማያውቅ በአጠቃላይ ዳግም የአገራችን ህዳሴ የሚያመለክት ብሩህ ተስፋ ሰጪ ዕድገት፣ ፍቅር፡ ህብር አንድነት  በመረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡

ይህን ያስቀናቸው ከሃድያን ይሁዳዎች ፊውዳል ፖለቲከኞች ለውጥ የማይሹ አንጃዎች  አገራቸውን ለባዕድ አሳልፈው ለመስጠት ደፋ ቀና በማለት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሁዳ ጌታን እንዴት አሳልፎ እንደሰጠው መፅሓፍ ቅዱስ ለሚያነብ መተረኩ ኣያስፈልግም፡፡  ይህች  በታሪኳ የገነነች  ታላቅ የጥቁር  ህዝብ  አኩሪ አገር  ከሃድያን ይሁዳዎች ደጅ ከሚጠኑባቸው  ህዝቦችና ኣገሮች  በፊት እስከ ኣሁን ድረስ  ነፃነትዋና ክብርዋ  አሳልፋ ያልሰጠች  ኩሩና  የኩሩዎች  አገር “ ዛሬ  ኑና ኣገራችንን አስተዳድርሉን ኣሉ፡፡“

ይሁዳ ጌታን  ለአይሁድ ካህናት  አሳልፎ  እንደሰጣቸው  የጌታውን ክብር እንደ ሸጠ  እነዚህም በህዝቦችዋ ህብር፣ ፍቅር፣ ኣንድነት  የፀናች፣  የባዕድ  ጠላቶችዋን መክታና አሳፍራ የመለሰች አገር “ኑና  አስተዳድሩን “  ማለት ክብርን  መሸጥ ማለት ነው  “ “እርስዎ አገራችን ቢመጡ ጠ/ሚኒስተር ወይ ፕሬዝደንት ኣድርገን እንሸሞት ነበር“ ኣሉ ለጌቶቻቸው ክብር ሲሰጡ ከሃዲዎች፡፡ ይሁዳም 30 ብር ብትሰጡኝ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ ነው ያለው ፡፡

የ21ኛው ክፍለ ዘመን ቅኝ ግዛት ናፋቂዎች የዓለም ህዝብ ከቅኝ ግዛት በተለቀቀበት ዘመን የኛውቹ  ፖለቲከኞች ቅኝ መገዛትን ናፈቁ፡፡

እኛ ጥቁር ህዝብ ጥቁር አፈር አንፀባራቂ ጀግንነት ያለን የሰው ልጅ መገኛ፣ የስልጣኔ ምንጭ  የመንፈሳዊና የቁሳዊ ቅርሶች ባለቤት  አገር ህዝብ ነን፡፡ ዛሬ በሰለጠነ ዘመን የሰው ልጅ  ማንነቱን ከመቼው በበለጠ ለማረጋገጥ ደፋ ቀና በሚልበት ዘመን  የኛዎቹ ፊውዳል ፖለቲከኞች  ዕድገትና ለውጥ በህይወታቸው ዘመን ያላዩና ያልሰሙ  በመሆናቸው ከግል ጥቅም  ይልቅ  መንፈሳዊ ቅናት የሌላቸው  የሃሊት እየተሽከረከሩ የበሉበት መሶብ  የረገጡ ምንደኞች  በፖለቲካ ፓርቲ  ስም የዋሁን ህዝብ ማወናበድ ተያያዙት፡፡ ኣገረሸባቸው ፡፡

ትናንት በህዝቦች ፍቃደኝነት የፀደቀው ህገ መንግስት በምርጫ ሰበብና የውጭ ጌቶቻቸው ተማምነው በሃይል ለመናድ ተንቀሳቅሰው ቤተሰቦቻቸውን ወደ ውጭ በመላክ ድሃውና የዋሁ ወጣት በገንዘብ ደልለው እንዲማገድ አደረጉ፡፡ መንግስት በወሰደው  ፍትሓዊ የማረጋጋት  ስልት  ሞንደኞቹ  በቁጥጥር ውለው በኣገራችን የህግ የበላይነት ተረጋገጠ ፡፡

ምስጋና ይድረሳቸውና የቁርጥ ቀን የአገር ሽማግሌዎች በወሰዱት የእርቅ ሽምግልና መንግስት እንደ በጎ እርምጃ  በመቁጠር  ሓሳባቸውን በመቀበል ወንጀለኞቹ ምህረት እንዲደረግላቸው ተደረገ፡፡ ይሁን እንጂ “ድመት መንኩሳ አመልዋ አትረሳ“ እንደሚባለው ህገ መንግስቱ አክብረው የህግ የበላይነት ተቀብለው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴያቸውን  ሳይገደብ  ሙሉ ምህረት ከተሰጣቸው  በኋላ ምህረት  የሰጣቸው  ህዝብ ትተው ወደ ጌቶቻቸው  አገር ሸሹ፡፡  ዳግም በህገ መንግስቱ  ጦርነት ኣወጁ፡፡ በየሴንተሩ ደጃፍ  መወደቅ ስራቸው ሆነ፡፡ ከለየላቸው የኢትዮጵያ አንድነት ጠላቶች  አበሩ ተባበሩ ፡፡  የአገራችን ክብር ለባዕድ አሳልፈው  ለመስጠት  ተደራደሩ፡፡ በአገር ውስጥ  የሚገኙ  የእነሱ ተቀጥያዎች በተራ ቃላት  ሊሸመግሉን ተጣደፉ ፡፡ “የ HR 2003 መሃንዲሶች ገንዘባቸው ንብረታቸው ነው የጠየቁት፡፡ ገንዘብህ ንብረትህ መጠየቅ ደግሞ ተገቢነው አሉ ፡፡“ ትልቅ ፍልስፍና ¡

“ እንኳን ሲሸጡን ሲያስማሙን እናውቃለን“ሲባል ኣልሰሙም ይሆና? ጌታም ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ሳያውቅ ቀርቶ ይሆን? የዘመናችን ይሁዳዎች በቃላት ሊሸመግሉን ለባዕድ ተፅዕኖ ሊዳርጉን በአንዲት ሉኣላዊት አገር የሞግዚት አስተዳደር ሊያስተዳደሩን ሊጬንብን በህጋችን በባህላችን በታሪካችን የነጭ ህግና ስርዓት ሊጫንብን ተዋከቡ፡፡ ዛሬማ “እኛም ነቅተናል ጉድጓድ ምሰናል” አለች አንዲት አንስሳ ሲባል ሰማችሁ?

ድሮ እንኳን ባልሰለጠነ ዘመን የውስጥ ጉዳያቸው በውስጥ ይዘው ጥቂቶቹ ከጠላት ጋር ቢያብርም በቁርጥ ቀን ግን ወደ አገራቸው እንደሚያደሉ የጠላት የጭቃ ውስጥ እሾህ እንደሚሁኑ “ በአድዋ ጦርነት ባሻ አውዓሎምን“ በሮም “ጐመራው ጀግናው ዘርኣይ ደረስን“ ማውሳቱ ትልቅ ምስክር ነው፡፡ የዘመናችን ከሃዲዎች ግን እንደ ነጋድራስ ኣፈወርቅ ገ/የሱስ በጥሩ ቃላት ከሽነው የጀግኖች አርበኞቹን ሞራል የሰለቡ ለባዕድ ያደሩ የአገር ፍቅር የሌላቸው ለምድ የለበሱ ተኩላዎች ናቸው፡፡ በተደራጁት ፓርቲ ስም ህዝብን በማተራመሳቸው በማሴራቸው በትእቢታቸው የባቢሎን ግንብ ጌታ እንደፈራረሰው ሁሉ ይሁዳዎቹም ፈራረሱ፡፡ እስከዚያኛው እርስ በርሳቸው ላይስማሙ ተስማሙ፡፡ ህዝባዊ መሰረት የሌለው ለግል ጥቅም የቆመ ድርጅት ውጤት ወድቀት መበታተን ነው፡፡

ትንሽ እንኳን ማሰብ ተስኖኣቸው የሃገር ሽማግሌዎችን ውለታ ዘነጉት “ለሰው ሞት ኣነሰው“ እንደሚባለው ሆነ፡፡ ዳሩ “ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል“ ነው፡፡ የስልጣን ጥማት ካላችሁ ህገ መንግስቱና የህግ የበላይነት አክብራቹህ አስከብራቹህ ተወዳድራቹህ ስልጠን መያዝ ህገ መንግስታዊ መብታቹህ ነው፡፡ ነገር ግን “ ኣውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱትም ኣይሰማም“ እንደሚባለው እንደ ካሃዲው ይሁዳ ውስጣቹህ በመሰሪ ተንኮል ተለብጦ ጥቁር ልባቹህና አእምሮአቹህ በይቅር ባዩ ህዝብና መንግስት ፊት መቆም ኣቃታቸህ፡፡ ሸሻቹህ፡፡ ይሁዳም በመጨረሻ የገጠመው ይህ ነው፡ በጌታ ፊት መቆም ኣቃተው፡፡ ቢሞትም መሬት ተፈችው ቢታነቅም ዛፍና ገመዱ ኣመፁበት አየሁን ሆኖ ሞተ፡፡

የእናት አገር ክህደትም የወገኑን የህዝቡን ጥቅም አሳልፎ የሰጠ ክቡርን ያዋረደ በምድርም በሰማይም እሞነት ቢስ ሆኖ እንደተባለው “ድመት መንኩሳ ኣመልዋን አትረሳ“ ከሆናቹ በመጨረሻው የይሁዳ ዕጣ አወዳደቅ ይሆናል፡፡

G/Tsadkan Kebede

Nov 16, 2006